# ዘልቀሽ እዩው

ተራራው፣ ቁልቁለት ሩቅ መንገድ ተጉዤ
ኣፈር፣ ኣቧራውን፣ ጭቅቅት ለብሼ
ስዞር፣ ስንከራተት ፍቅርን ፍለጋ
ብዙ ኣሳልፌያለሁ ስንት ዓይነት ኣደጋ
ቆምያለሁ ከደጅሽ ከስቹ፣ ጠቁሬ
ማየት ተስኖኛል ዓይንሽን ደፍሬ
ከጭቅቅቱ ውስጥ ታዩው ይሆን ፍቅሬ!

ኣፈር፣ ኣቧራውን የምሸከመው
ሁሉን ውጣ ውረድ የማሳልፈው
ታውቂ ይሆን ወይ ውዴ ላንቺ ብየ ነው
ተመልከቺው ልቤን በልብስ ኣትፍረጂ
ቀረብ ብለሽ እዩኝ ከሮቁ ውረጂ
በቆሻሻው ልብሴ ኣይታለል ዓይንሽ
ፍቅሬን እዩውና፣ ክፈችልኝ ልብሽ።

ገ/ኢ. ጐርፉ።

Back to Meskot

---

*The views reflected in the above poems are solely of the author and are not necessarily shared by Meskot. You may contact G.E. Gorfu for comments at gegorfu@yahoo.com.*